# ፖሊሲ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ የመረጃ ምንጭ:** ABA, ABC, ACA, AEB, GEG-RA, IFA, IFA-RA, IKC-RA, ISB-RA, JEA-RA
**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፦** የሥርዓተ ትምህርት እና የማስተማሪያ ፕሮግራሞች

## የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (ሃይስኩል) ትምህርት ማዕቀፍ እና መዋቅር

A. **ዓላማ**

የሜሪላንድ ስቴት የመመረቂያ መስፈርቶችን የሚያሟላ እና ከዚያም ያለፈ፣ ሁሉንም ተማሪዎች ለድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ለስራ ቦታ የሚያዘጋጅ፣ እና ተማሪዎችን መረጃ እንዲሰበስቡ እና እንዲጠቀሙ የሚያስችል ችሎታና ክህሎትን የሚፈታተን፣አዲስና ከባድ ተግባር ለማከናወን ፍላጎትን የሚቀሰቅስ እና ሁሉን አቀፍ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ለማቅረብ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ያለውን ቁርጠኝነት ማረጋገጥ እና ችግሮችን ለመፍታት እና በህዝብ እና በግል ጉዳዮች ላይ በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ ለመስጠት ከሌሎች ጋር እንዲተባበሩ ተማሪዎችን ማዘጋጀት/በእውቀት ማስታጠቅ።

ለሥራ ባልደረቦች እና ለማህበረሰቡ ስለ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አደረጃጀት እና የትምህርት መርሃ ግብሮችን አቀራረብ መመሪያ መስጠት፣ለወጣቶች እና ጎልማሶች ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ እድገትን የሚደግፉ አካባቢዎችን በመፍጠር ከሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የአካዳሚክ ስኬት ከፍተኛ ተስፋ መመሪያ መስጠት።

B. **ጉዳዩ**

ለኮሌጅ ስኬት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዝግጅት ወሳኝ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁሉም ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና በስራ አለም ለስኬት የሚያዘጋጃቸውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ይጠብቃል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ለእያንዳንዱ ተማሪ ስኬትን በጠንካራ፣ ሁሉን አቀፍ ሥርዓተ ትምህርት ያቀዳጃል። ፍላጎቶችን፣ ግቦችን እና የወደፊት እቅዶችን ግልጽ ለማድረግ ለተማሪዎች ተገቢ እድሎች፣ ብቃት ያለው እና ቁርጠኛ ሰራተኛ እና አመራር፣ የትብብር እና እንደሁኔታው የሚስተካከል ድርጅታዊ መዋቅር፣ በተለየ ሁኔታ የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች፣ እና ወላጅ/አሳዳጊ እና የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላትን በንቃት ያሳትፋል።

C. **አቋም**

1. በትምህርት ቤት ያለው ባህል

   የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁሉም ተማሪዎች የዕድሜ ልክ የመማር ክህሎት እንዲኖራቸው እና እንዲያዳብሩ፣ የወደፊት ስኬታማነትን እንዲያስሱ እና እንዲያሰላስሉ፣ እና ከድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህይወት ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ ወጥነት ያለው ከፍተኛ ተስፋ እንደሚጣልባቸው ከተማሪዎች ይጠበቃል።

   a) የሥራ ባልደረቦች ሁሉም ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ መማር እንደሚችሉ እና ተማሪዎችን በሙሉ አቅማቸው እንዲያሳኩ መጠበቅ እና ማበረታታት እንደሚችሉ ያምናሉ።

   b) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማህበረሰብ ለፍትሃዊነት ቁርጠኛ ነው፣ ብዝሃነትን ይመለከታታል፣ እና የተማሪ ስኬት በግለሰብ ተጨባጭ ወይም በሚታዩ ግላዊ ባህሪያት መተንበይ አግባብነት

እንደሌለው የውጤታማነት እንቅፋቶችን ለማስወገድ፣በቦርድ ፖሊሲ ACA፣መሠረት አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃትየሠፈነበት አሠራር እንዲሰፍን በንቃት ይሠራሉ።

c) በማስተማር ተግባር እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች፣ ተማሪዎች ለጤናማ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አእምሮአዊ እድገት አስፈላጊ የሆኑትን ግለሰባዊ ችሎታዎች ይማራሉ። የትምህርት ቤት ድባብ እያንዳንዱ ተማሪ በትምህርት ቤቱ ውስጥ በአንድ ወይም በብዙ አዋቂ ሰዎች በደንብ እንዲታወቅ ያበረታታል እና ብዙ እድሎችን ይሰጣል።

d) የት/ቤት መሪዎች በተማሪዎች፣ በሰራተኞች እና በማህበረሰቡ አባላት መካከል አስተማማኝ የትምህርት ቤት ድባብ እና አወንታዊ ግንኙነቶችን እንዲተገበር ያደርጋሉ/ያበረታታሉ። የት/ቤት መሪዎች ለተማሪዎች እና ለሰራተኞቻቸው ግልጽ የሆኑ የባህርይ ፍላጎቶችን ያስተጋባሉ።

e) ሰራተኞች፣ ቤተሰቦች እና የማህበረሰብ አባላት ለተማሪ ስኬት አብረው ይሰራሉ።

(1) የት/ቤት ሰራተኞች በተቻለ መጠን በማህበረሰቡ ውስጥ በሚነገሩ ቋንቋዎች ከማህበረሰቡ ጋር ግንኙነትን ያመቻቻሉ።

(2) በመደበኛነት የተማሪ መገኘትና ትምህርት የመከታተልን አስፈላጊነት ለማጉላት የትምህርት ቤት ሰራተኞች ከተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር አብሮ መሥራት ጥራት ያለው የመማር ልምድ አስፈላጊ አካል ነው።

(3) የት/ቤት መሪዎች የተማሪዎችን፣ የሰራተኞችን እና የማህበረሰቡን ስኬቶችን ይገነዘባሉ እና ያከብራሉ።

(4) ሰራተኞች፣ ቤተሰቦች እና የማህበረሰብ አባላት ለአገልግሎት እና በተግባር ላይ የተመሰረተ ትምህርት፣ እንደመምህር ወይም የታመነ አማካሪ በመሆን ለሙያ ሥራዎች/አክቲቪቲዎች መርጃዎችን (ሪሶርሶችን) እና አማራጮችን ይሰጣሉ።

f) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሰራተኞች፥ ለተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በኋላ ያሉትን አማራጮች በሚመለከት፣ ስለሚያስፈልጉ ዝግጅቶች እና የሚያገኙትን እርዳታ ጭምር እንዲያውቁ ድጋፍ ይሰጣሉ፣ በዚህም ተማሪዎች በወቅቱ የሚያጠኑትን ትምህርት ከወደፊት ጥረታቸው ጋር ያገናኛሉ። ሰራተኞች በሚከተለው መልኩ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ይሰጣሉ።

(1) ተማሪን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አመታት የሚያሸጋግረውን የጥናት ኮርስ እና ተዛማጅ ተግባራትን ለማቀድ ከእያንዳንዱ ተማሪ ጋር ይሰራሉ፣ እና አካዳሚያዊ እና ግላዊ ግቦችን ለማሳካት የሚያስፈልጉትን ኮርሶች ይዘረዝራሉ። MCPS ደንብ ISB-RA መሠረት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መመረቂያ መስፈርቶች ላይ እንደተገለጸው ተማሪዎች ከ 8ኛ ክፍል በላይ ያለውን የትምህርት መርሃ ግብር በአጥጋቢ ሁኔታ ማጠናቀቅ አለባቸው።

(2) ተማሪዎች ከፍላጎታቸው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጠንካራ ኮርሶች እንዲወስዱ እና የድህረ- ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ግባቸውን ለማሳካት እንዲዘጋጁ ያበረታቷቸዋል።

2. *ሥርዓተ ትምህርት፣ ማስተማር እና ግምገማ*

MCPS የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስርአተ ትምህርትን፣ ማስተማር እና ምዘናን ተግባራዊ ያደርጋል ለሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከፍተኛ ጠንካራ ትምህርት መጎናፀፋቸውን ማረጋገጥ እና ወጣት ጎልማሳ ተማሪዎችን ልዩ እና እንደፍላጎታቸው የሚመቻች ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ጥረት ያደርጋል።

a) ስርአተትምህርት

(1) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ካሪኩለም የቦርዱን እና የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) የመመረቂያ መስፈርቶችን ያሟላል። ቦርዱ ሁሉንም ተማሪዎች የሚጠቅም መሆኑ ሲታወቅ ከስቴት ዝቅተኛ መስፈርቶች በላይ መስፈርቶችን የመተግበር ስልጣን አለው። MSDE ለመመረቂያ 21 ክሬዲቶችን ይፈልጋል፣ ከነዚህም 18 ክሬዲቶች በተወሰኑ ኮርሶች መገኘት አለባቸው። MCPS ለመመረቂያ 22 ክሬዲቶች የሚያስፈልጉ ሲሆን ከነዚህም 19.5 በተወሰኑ ኮርሶች ማግኘት አለባቸው፣ በሂሳብ እና ተጨማሪ ክሬዲት በአካል ብቃት ትምህርት ግማሽ ክሬዲት፣ MCPS ደንብ ISB-RA በተገለፀው መሠረት፥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መመረቂያ መስፈርቶች።

(2) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ ሥርዓተ-ትምህርት የትምህርት ግቦችን ለማሣካት የስቴት እና የብሔራዊ ስርአተ ትምህርት ደረጃዎችን ያሟላል። የጥናት መርሃ ግብሩ የሁሉንም ተማሪዎች ችሎታቸውን እና ብቃታቸውን ለመፈተሽ የተለያዩ የመማሪያ ተሞክሮዎችን በማቅረብ ለድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ለስራ መስኮች ስኬታማ እንዲሆኑ ያዘጋጃቸዋል። ስርአተ ትምህርቱ ከቦርድ ፖሊሲ IFA፣ ስርአተ ትምህርት እና MCPS ደንብ IFA-RA ስርአተ ትምህርት ጋር በሚጣጣም መልኩ ይገመገማል።

(3) በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠቃላይ የጥናት መርሃ ግብር "comprehensive program of studies" ይሰጣል። ቦርዱ በምድብ 1 የተወሰኑ አስፈላጊ ኮርሶች በሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመደበኛነት መሰጠታቸውን ያረጋግጣል። ቦርዱ የምድብ 1 ኮርሶችን ስርአተ ትምህርት ይገመግማል፥ እንዲሁም የትምህርት ስርዓት-አቀፍ የምዘና ደረጃዎችን መከተሉን ያረጋግጣል። ሁሉም አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች MSDE እና MCPS በአራት ዓመታት ውስጥ የሚፈለጉትን የመመረቂያ ክሬዲቶች እንዲያገኙ የሚያስችል ተገቢ የሆነ የምድብ 1 ኮርሶችን ይሰጣሉ።

(4) ቦርዱ ተጨማሪ ኮርሶችን እንደ ምድብ 2 አጽድቋል። የምድብ 2 ኮርሶች በአንድ የትምህርት ዓይነት ውስጥ የተማሪን ግንዛቤ ለማስቀጠል፣ ለማስፋት እና ለማበልጸግ አስፈላጊ ናቸው። በተጨማሪም፣ የምድብ 2 ኮርስ የመመረቂያ መስፈርት ሊያሟላ ይችላል። እነዚህ ኮርሶች የሚሰጡት የተማሪ ፍላጎት፣ የሰው ሃይል እና የበጀት ፍቃድ ሲኖር ነው።

(5) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የኮርሶች ዝርዝር መግለጫ/ቡለቲን ውስጥ ሁሉም የምድብ 1 እና 2 ኮርሶች ተዘርዝረዋል/ተገልጸዋል።

(6) MCPS Regulation ISB-RA፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መመረቂያ መስፈርቶች ላይ በተገለጹት ሁኔታዎች መሰረት የታቀዱ እና የፀደቁ ከሆነ፤ ተማሪዎች ከ MCPS ውጪ ባሉ ተቋማት በኮርስ ስራ ያገኙትን ክሬዲት ሊያመለክቱ ይችላሉ።

b) ትምህርት አሰጣጥ

የማስተማር ተግባሮች ላይ ተማሪዎች ንቁ እና ቀልጣፋ ተማሪዎች እንዲሆኑ የሚያበረታቱ የተለያዩ ዘዴዎችን፣ ስልቶችን እና ግብዓቶችን ያካትታሉ።

(1) የማስተማር ተግባሮች ከቦርድ ፖሊሲዎች እና ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

(MCPS) እንደ የቦርድ ፖሊሲዎች IKA ከመሳሰሉት ደንቦች ጋር በተጣጣመ መልኩ፣ የትምህርት ውጤት መስጠት እና ሪፖርት ማድረግ፣ IOA፣ ተሰጥዖ እና ከፍተኛ ችሎታ ላላቸው ትምህርት፣ IOD፣ የእንግሊዝኛ ትምህርት ለእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች፣ IOB፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርት፣ እና MCPS ደንብ IHB-RA፣ በትምህርት ቤት በአካዳሚክ ዝንባሌ የመመደብ ተግባሮች።

(2) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትምህርት ተማሪዎችን መረጃን እንዲገነዘቡ/እንዲረዱ፣ እንዲሰበስቡ፣ እንዲገመግሙ፣ እና እንዲያዋህዱ እና ችግሮችን ለመፍታት ከሌሎች ጋር እንዲተባበሩ ያዘጋጃቸዋል። የሥራ ባልደረቦች ተማሪዎችን እንደሚከተለው ያዘጋጃሉ፦

(a) ተማሪዎች ስኬታማ ለመሆን ከፍተኛ ተስፋ እንዳላቸው የሚጠበቅባቸው መሆኑን ይገልጹላቸዋል።

(b) ጥልቅ አስተሳሰብን የሚያዳብሩ እና ተማሪዎችን ንቁ፣ ተሳታፊ እና የዕድሜ ልክ እውቀት የሚገበዩ ተማሪዎች እንዲሆኑ የሚያበረታታ ቴክኖሎጂን ጨምሮ የተለያዩ አዳዲስ እና በጥናት ላይ የተመሰረቱ ዘዴዎችን፣ ስልቶችን እና ግብአቶችን ያካትታሉ።

(c) የተመደበውን የማስተማሪያ ጊዜ በብቃት እና በውጤታማነት ይጠቀማሉ።

(d) ለተማሪዎች የመሪነት እድሎችን መስጠት እንዲሁም ለተማሪዎች ስለ ንግግር እና በውጤታማነት ራስን መግለጽ ያለማምዳሉ።

(e) ፈጣን፣ የዳበረ፣ የትምህርት ድጋፍ እና የተመቻቹና የተለያዩ የማስተማሪያ እድሎችን እና ግብዓቶችን እንደአግባቡ በማቅረብ ተማሪዎች የአካዳሚክ አቅማቸውን አሟልተው እንዲሠሩና ትምህርት መቅሰም እንዲችሉ ይረዷቸዋል።

(f) በማቀድ እና በማስተማር ሂደት ውስጥ የሁሉንም የአጠቃላይ መደበኛ ትምህርት፣ አማራጭ ትምህርቶች፣ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች እንግሊዝኛ ትምህርት (ESOL) እና የልዩ ትምህርት ሰራተኞች ልዩ ችሎታቸውን እና ክህሎቶቻቸውን ይጠቀማሉ።

c) *ግምገማ*

በቦርድ ፖሊሲ IKA ላይ እንደተገለጸው የትምህርት ችሎታ ምዘና፣ ውጤት መስጠት እና ሪፖርት ማድረግ፣የማስተማር ዑደቱ ዋና አካል ነው። ከዲስትሪክት፣ ስቴት እና ከሀገር አቀፍ ደረጃዎች ጋር የተሳሰለ አጠቃላይ የምዘና ፕሮግራም የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

(1) ለተማሪዎች እና ለወላጆች/አሳዳጊዎች የሚጠበቅባቸውን ነገሮች በግልፅ እና ጊዜውን በጠበቀ ሁኔታ እንዲያውቁት የሚደረጉ የውጤት መስፈርቶች።

(2) የትምህርት ግቦችን ለማሳካት የማስተማር ሁኔታን ለማቀድ እና ትምህርት ለመስጠት የሚያገለግሉ ቅድመ-ግምገማዎች፣ ፎርማቲቭ ምዘናዎች፣ እና የማጠቃለያ ምዘናዎች፣ ለተማሪዎች ስለ አፈፃፀማቸው ትርጉም ያለው እና ወቅታዊ ምላሽ እና ተማሪዎቹ ከትምህርታቸው ያገኙትን እውቀት እንዲያሳዩ የተለያዩ እድሎችን ይሰጣሉ።

(3) ውጤታማ የማስተማር እና የመማር ሂደትን ለማሻለጥ በማስተማር ዑደት ውስጥ

እንደገና ማስተማር እና መገምገም።

(4) የተማሪዎችን ውጤት ለተማሪዎች፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ለመምህራን፣ ለአስተዳዳሪዎች እና ለትምህርት ስርዓት ቀጣይነት ባለው መልኩ ወቅታዊ ሪፖርት ማድረግ።

(5) ትምህርት ቤቶች በተናጠል እና በትምህርት ቤቶች መካከል ወጥነትን ማረጋገጥ።

3. ድርጅታዊ መዋቅር

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተዳዳሪዎች ከት/ቤት አመራር ቡድኖች፣ሰራተኞች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ተማሪዎች እና ከማህበረሰቡ ጋር የት/ቤታቸውን ድርጅታዊ መዋቅር እና የማሻሻያ እቅዶችን በተመለከተ የትምህርት ስርአት ቅድሚያ ትኩረት ጋር አብረው ይሰራሉ። ትምህርት ቤቶች ለመማር እና ለማስተማር የተለያዩ መዋቅሮችን በመተግበር ከፍተኛ ስኬትን ያስተጋባሉ።

a) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መሪዎች እንደሁኔታው አመቺ መርሐ ግብሮችን በመጠቀም የተማሪዎችን ስኬት የሚያበረታታ፣ የተማሪዎችን ሽግግር የሚያቃልሉ እና የፕሮግራም ቀጣይነትን የሚያመቻቹ ንቁ እና ትርጉም ያለው የትምህርት ተሞክሮዎችን ለማቅረብ ሪሶርሶቻቸውን ያሳድጋሉ።

b) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መሪዎች የተማሪን ስኬት የሚያበረታታ፣ ለተማሪ ፍላጎቶች ምላሽ የሚሰጡ እና በተማሪዎች እና በሰራተኞች መካከል አወንታዊ ተሳትፎን የሚያበረታቱ ማህበረሰቦችን በትምህርት ቤት ውስጥ ያዳብራሉ።

c) የተለያዩ የትምህርት ፍላጎቶች ላሏቸው ተማሪዎች ተገቢውን የትምህርት እድል ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሰው ሃይል ያለው እና የተደራጀ ነው።

d) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መሪዎች የሚከተሉትን ለማሳካት መምህራን ጊዜአቸውን በብቃት እና በውጤታማነት እንዲጠቀሙ እድል ይሰጧቸዋል፦

(1) የትምህርት አሰጣጥ እና ግምገማን ማቀድ እና ማስተባበር።

(2) የተማሪዎችን የትምህርት ግስጋሴ ይቆጣጠራሉ፣ከተማሪዎች ጋር ይገናኛሉ፣ እና ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ይነጋገራሉ።

(3) በሙያዊ ትምህርት እና ሌሎች የሙያዊ እድገት እድሎች ውስጥ ይሳተፋሉ።

e) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሰራተኞች በተማሪዎች የትምህርት ቀን የማስተማሪያ ጊዜን በብቃት ይጠቀማሉ።

f) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሰራተኞች ከትምህርት ቤት በፊት እና ከትምህርት በኋላ የተራዘመ የትምህርት ጊዜ እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎችን ለማጎልበት እና ለአካዳሚክ ድጋፍ እድሎችን ይሰጣሉ።

g) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሰራተኞች የሙያ ትምህርት ማህበረሰቦችን እውቀት ለማጎልበት እና በተማሪዎች፣ በመምህራን፣ በወላጆች/አሳዳጊዎች እና በሌሎች የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት መካከል ውጤታማ ግንኙነቶችን ለማመቻቸት የመገናኛ መሳሪያዎችን በብቃት ይጠቀማሉ።

4. አመራር እና እቅድ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተዳዳሪዎች እና የት/ቤት አመራር ቡድኖች ለሁሉም ተማሪዎች ስኬትን ለማረጋገጥና ውጤታማ የትምህርት ማህበረሰብ ለመፍጠር፣ ለመምራት፣ ለማስተዳደር እና ለፈጠራ ያላቸውን ፍላጎት ለማነሳሳት ከሰራተኞች፣ ከተማሪዎች፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች እና ከማህበረሰቡ ጋር በትብብር ይሠራል። ውጤታማ የትምህርት ቤት መሪዎች

a) ለአስተዳዳሪዎች፣ ለመምህራን እና ለድጋፍ አገልግሎት ሠራተኞች የሙያ ዕድገት ሥርዓትን መመዘኛዎች ሞዴል ማድረግ።

b) በተማሪዎች መካከል ያለውን የውጤት ክፍተት ለማስወገድ ትምህርቱን የሚያዘጋጅ እና ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁ እንዲሆኑ የተዘጋጀውን ጥብቅ የማስተማሪያ ፕሮግራም መምራት እና መተግበሩን መቆጣጠር።

c) የማልኮም ባልድሪጅ የትምህርት መስፈርት "Malcolm Baldrige Education Criteria" ስለ ትምህርት አፈጻጸም የላቀ ቀጣይነት ያለው መሻሻል እና መተግበርን ማመቻቸት።

d) የተማሪዎችን አካዴሚያዊ እና ግለሰባዊ ፍላጎቶች፣ የት/ቤቱን አቅጣጫ እና ወደተጠቀሱት ግቦች ለመድረስ የጋራ ራዕይን ለማዳበር እና ለመተግበር ከሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ከማህበረሰቡ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ይተባበራል።

e) በትምህርት ቤቱ ውስጥ አመራርን ማዳበር እና ሰራተኞችን፣ ተማሪዎችን፣ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ማህበረሰቡን በውሳኔ አሰጣጡ ሂደት ላይ ማበረታታት።

f) አስተማማኝ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የመማሪያ አካባቢን ለማረጋገጥ አደረጃጀትን፣ ኦፕሬሽኖችን እና ሃብቶችን በፍትሃዊነት ማስተዳደር።

5. የወላጅ/አሳዳጊ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ግንኙነት

ከቦርድ ፖሊሲ ABA በተጣጣመ መልኩ፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ እና የቦርድ ፖሊሲ ABC፣ የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ማህበረሰቡ ለተማሪዎች ማህበራዊ እና አእምሯዊ እድገት ደጋፊዎችና አጋሮች ናቸው።ይህ አጋርነት የሚከተሉትን ያካትታል፦

a) በቤተሰቦች እና በትምህርት ቤት ሰራተኞች መካከል ያለው ግንኙነት የአንድን ተማሪ የትምህርት ተሞክሮ፣ የተማሪውን ትምህርት ከት/ቤት ውጭ ለመደገፍ ትብብር በማድረግ፣ እንዲሁም ቤተሰቦች በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች እና ዝግጅቶች ላይ እንዲሳተፉ ያሉትን ዕድሎች በተመለከተ መረጃ ለመስጠት እና ግብአቶችን እና ግብረመልስ መለዋወጥ።

b) በቦርድ ፖሊሲ AEB መሠረት፣ ለቀጣይ መሻሻል ስትራቴጅካዊ እቅድ ለማውጣት በትምህርት ቤት ማሻሻያ ቡድኖች እና ሌሎች ለት/ቤቱ አቅጣጫ በሚያዘጋጁ የአማካሪ ቡድኖች ውስጥ የወላጅ/አሳዳጊ፣የተማሪ እና የማህበረሰብ ተሳትፎን ማጠናከር።

c) ከወላጅ/አሳዳጊ/ከመምህራን/ከተማሪዎች ድርጅቶች፣ ከማህበረሰቡ ጋር፣ ከንግድ ድርጅቶች እና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ከውጪ ያለ ሀብት ወደ ትምህርት ቤት በማምጣት፣ በትምህርት እና በሙያ መካከል ቀጥተኛ ትስስር ለመፍጠር እና ለተማሪዎች ተሳትፎ ትክክለኛ እድሎችን ይሰጣል።

d) ስለ ቦርድ ፖሊሲዎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች እና ተግባሮች

የወላጅ/አሳዳጊ ማቀንቀን እና ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ማድረግ።

6. ሰብአዊ ሪሶርስ እና ሙያ ማዳበር

MCPS ስኬትን ለማሳደግ እና የሁሉንም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት እውቀት እና ክህሎት ያላቸውን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሰራተኞችን ይመለምላል፣ ይቀጥራል እና በሥራ ላይ የመቆየት እድል ይኖራቸዋል። የ MCPS ሙያዊ እድገት ስርዓት ለሁሉም አስተዳዳሪዎች፣ አስተማሪዎች እና የድጋፍ አገልግሎት ባለሙያዎች እውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውን እና አቅማቸውን እንዲያዳብሩ የመማር ማስተማር ሂደቱን ያለማቋረጥ ለማሻሻል መደበኛ እና ስልታዊ እድሎችን ይሰጣል።

a) የሥራ ባልደረቦች ስለ ጉርምስና/ኮረዳነት እድገትና ባህሪያት እውቀት ያላቸው ስለሆኑ ተማሪዎች ስለሚጠበቅባቸው ከፍተኛ ተስፋ ለሁሉም ያስተላልፋሉ።

b) የት/ቤት ሰራተኞች ከተማሪዎች እና ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር አወንታዊ ግንኙነቶችን በማዳበር እና በመማር ሂደት ውስጥ በማሳተፍ የተካኑ ናቸው።

c) የት/ቤት ሰራተኞች የትምህርት ይዘት እውቀትን የተካኑ ስለሆኑ ውጤታማ ትምህርት ይሰጣሉ።

d) የሰራተኞች ስብጥር በተቻለ መጠን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተለያየ ማህበረሰብን ብዝሃነት ስብጥር ያንፀባርቃሉ።

e) የሰራተኞች ምልመላ ሲደረግ የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት የግል ፍላጎቶች ይመለከታል።

D. **ተፈላጊ ውጤቶች**

1. በአካዳሚክ ልቀት ላይ የሚያተኩር የትምህርት ፕሮግራም።

2. ተማሪዎች የመመረቂያ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ እና ዝንባሌአቸውን በተመረጡ ኮርሶች እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች እንዲያስሱ የሚያስችል ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ የሆነ አጠቃላይ ፕሮግራም ነው።

3. ተማሪዎች በድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና በስራ አለም ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያዘጋጃቸው ፕሮግራሞች፣ ኮርሶች፣ እንቅስቃሴዎች እና የመማሪያ ልምዶችን ይሰጣል።

4. በተማሪዎች፣ በሰራተኞች፣ በወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና ቤተሰቦች መካከል ትብብር እና የአካዳሚክ ስኬትን እና የተማሪዎችን አእምሯዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ እድገት ለመደገፍ።

5. የአእምሯዊ እድገትን እና የባለቤትነት ስሜትን የሚያበረታታ እና በተማሪዎች መካከል ዜግነትን፣ ኃላፊነትን እና መከባበርን የሚያበረታታ ባህል እንዲሰፍን ጥረት ማድረግ።

6. መረጃን ለመሰብሰብ እና ለመጠቀም እና ከሌሎች ጋር በመተባበር ችግሮችን ለመፍታት እና በህዝብ እና በግል ጉዳዮች ላይ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት ብቃት ያላቸው ተመራቂዎች።

E. **ግምገማና ዘገባ**

ይህ ደንብ በቦርድ ድህረ እይታ ሂደት ይገመገማል።

**ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች**: Annotated Code of Maryland, Education Article §7–205, Code of

**የፖሊሲው ታሪክ፡**በውሳኔ ቁጥር 348-88፣ ጁን 27, 1988 በሥራ ላይ ዋለ። በውሳኔ ቁጥር 567-10፣ዲሴምበር 7 ቀን 2010፣ በውሳኔ ቁጥር 319-17፣ ጁን 26, 2017 ቴክኒካዊ ማሻሻያዎች ተደርገዋል።

**ማሳሰቢያ፡** ከውሳኔ ቁጥር 348-88 በፊት፣ ይህ ርዕስ የተደነገገው እንደሚከተለው ነበር፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፖሊሲ፣ በውሳኔ ቁጥር 161-80፣ ፌብሩወሪ 12, 1980 ጸደቀ። በውሳኔ ቁጥር 912b-83፣ ኖቬምበር 8, 1983 ተሻሽሏል። በውሳኔ ቁጥር 333-86፣ ጁን 12, 1986 እና በውሳኔ ቁጥር 458-86፣ ኦገስት 12, 1986 ተሻሽሏል፤ በውሳኔ ቁጥር 348-88 ጁን 27 ቀን 1988 ተሽሯል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፦ ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፦ U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፦ 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ጁን 2022